# የመለስ አምልኮን በጨረፍታ
## ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ (ክፍል ሁለት )

ዮናስ 7/13/12

በፍትህ ጋዜጣ አንድ በሉ አምድ ስር የጋዜጣዋ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ዳሳለኝ የሚጽፋቸውን መጣጥፎች የመለስ አምልኮ በሚል ርዕስ በመጽሃፍ መልክ አሳትሞ ለንባብ አብቅቷል፡፡ ምንም እንኳ ጽሁፎቹ በጋዜጣዋ በኩል ለንባብ የበቁ ቢሆንም በመጽሃፍ መልክ ዳግም ለንባብ ሲበቁ (ተመስገን ህዝቡ ስለወተወተኝ ነው ቢልም) የተለየ እና ድብቅ አላማ እንዳለው በመገንዘብ በአምስት ክፍል የተሰናዳውን የመጣጥፍ ጥርቅም በወፍ በረር መመልከቱ ተገቢ ሆኖ ስላገኘሁት፤ በሌላ በኩል ደግሞ "ፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ" በሚል ርዕስ በ6 ተከታታይ ክፍል ካቀረብኳቸው መጣጥፎቼ ጭብጥ ጋር ጥርቅሙ ተያያዥ ሆኖ ስላገኘሁት ዳግም ይህን አጀንዳ ለማንሳት መፍቀዴን በክፍል አንድ ጨረፍታዬ መግለጼ ይታወሳል፡፡

እነሆ ሁለተኛውን ጨረፍታ ከመጻፌ በፊት ግን የተመስገን ደሳለኝን ገመና ባየንበት ክፍል አንድ ጨረፍታዬ ላይ ብዙ የተምታቱ የተጣረሱና ከራሱ ሃሳብ ጋርም ጭምር እዛው በዛው ገጽ ሳይዘል እንደሚጋጭ አውስተናል፡፡ የግጭቱ መንስኤ ደግሞ የዜሮ ድምር ፖለቲካ አስተሳሰብ ተፈጥሮና ውጤት መሆኑንም ተመልክተናል፡፡

ይህንኑ የተምታታ የዜሮ ድምሩ ስብስብ አስተሳሰብ በሁለተኛው ጨረፍታዬ ከመቀጠሌ በፊት ግን ጨረፍታዬን የሚያጠናክርልኝ፣ የተመስገንን ነፃ ጋዜጠኛ ያለመሆንና ያለፈውን ሥርዓት ናፋቂ መሆኑን የሚያረጋግጥልኝ ባጠቃላይ ለጨረፍታዬ አጽንኦት የሚሆነኝን ጉዳይ ከፍትህ ጋዜጣ የሴኔ 29/2204 እትም ላይ እንደመግሚያ በመውሰድ ወደ አጀንዳዬ ብመለስ አይከፋም፡፡

"ይቅርታ" የኢህአዴግ ቃጭል ወይስ?. . . . " ይላል ርዕሱ፤ ተመስገን "ነፃ" ጋዜጠኛ መሆኑን በተደጋጋሚ ይነግረናል፤ በዚህ ብቻም ሳያበቃ ከዚህ ቀደም ስለነበሩት ጋዜጦችና ጋዜጠኞችም "ነፃ" ናቸው ሲል ከመናገር ተቆጥቦ አያውቅም። ነገር ግን እሱም ሆነ መሰሎቹ ነፃ አይደሉም፤ የአንድ ወገን አራጋቢ ብቻ ሳይሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲ አባልም ናቸው ለማለት የሚያስደፍረን በርካታ መገለጫዎች አሉ ስል በፍትህና አምደኖቹን ጨረፍታዬ ሞግቼ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ለሙግቴ ተጨማሪ ማጠናከሪያ የሚሆንልኝን ደግሞ "ይቅርታ" የኢህኤደግ ቃጭል? ወይስ . . ." ከሚለው የተመስገን መጣጥፍ እነሆ፡፡

"እንዲህ ውጥረት በነገሰበት አንድ ቅዳሜ ከቅንጅቱ ዋነኛ አመራሮች አንዳቸውን በአካል ልተዋወቅ ወደ ቀጠሮ ቦታ እየሄድኩ ነው፡፡ መስከረም 28 ቀ 1998 ዓ.ም፡፡ በምርጫው ላይ የጎላ ተሳትፎ

የለኝም ፡፡ የየትኛውም ፓርቲ አባል አይደለሁም፡፡ድምጼንም ለማንም አልሰጠሁም፡፡ ነገር ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ እልፍ አእላፎችን ከጎኑ ማሰለፍ ከቻለው “ቅንጅት” መሪዎች አንዳቸውን ልተዋወቅ ነው፡፡ የሚያስተዋውቀኝ ደግሞ በእጅጉ የማከብረውና የማደንቀው ወዳጃችን አብይ ተክለማርያም ነው፡፡ . . . . ንግግሯ በደስታ ሞላኝ” አብይ ተክለ ማርያም በወቅቱ መዝናኛ በምትል ጋዜጣው ከማዝናናት ወጥቶ የቅንጅቱ አንድ ክንፍ ሆኖ ይሰራ የነበረ "ጋዜጠኛ" ነው፡፡ ተመስገን ደግሞ "ጋዜጠኛ" ከነበረ ብርቱኳን ጋር ለዘገባ ቢሄድ ባልከፋ፤ በአካል ሊተዋወቅ ሄደ፤ ንግግሯም በደስታ ሞላው፡፡ በደስታ የተሞላው ነፃ ጋዜጠኛ  ደግሞ ዛሬም ድረስ የቅንጅቱ እንጀራ ልጅ ለሆነው አንድነት ልሳን ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

ይህ እንዳይታወቅበት ሲል እና ድምጽ በመስጠቱ የተቀጣ ያለ ይመስል፣ ለማንም  ድምጽ አልሰጠሁም፣  የማንም ፓርቲ አባል አይደለሁም ወዘተ ይለናል፡፡ እነ አብይ ዛሬ በሽብርተኝነት ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ በሌሉበት ያገኙ ግለሰቦች ናቸው። በአዲስ ነገርም ላይ የነበራቸውን ነገር እናስታውሳለን። አሁን ደግሞ በአዲስ ነገር ኦን ላይን ምን እየጻፉ እንደሆነም እናውቃለን፡፡ የሚጽፉት ሁሉ ሽብርተኝነትን የሚደግፍ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ናቸው ሲል ብያኔውን ሰጥቷል፡፡ ነፃ ነኝ የማንም አይደለሁም የሚለው ተመስገንም እነዚህን ግለሰቦች በእጅጉ የሚያከብራቸው ወዳጆቹ ናቸው፡፡ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉ ደግሞ ከሽብርተኞች ጋር መወዳጀት.... ይለናል፡፡ ብርቱካንን  ሊተዋወቅ ሄዶ በደስታ ተሞላሁ የሚለን ተመስገን ተመልሶ ነፃ ጋዜጠኛ ነኝ ቢለን በኔ በኩል አይገባኝም፡፡ አሁን ወደ አጀንዳችን ተመልሰናል፡፡

የመጣጥፍ ጥርቅሙ ሁለተኛ ክፍል "ይድረስ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዜናዊ “መለስ ዜናዊ ከመይ ቀኒዮም” የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል፡፡ በሀገራችን ፍርድ ቤት የለም ፤ፍርድ ቤቶች ሁሉ “የካንጋሮ ፍርድ ቤቶች ናቸው” "የተሰጣቸውን የሚወስኑ አሻንጉሊቶች" ወዘተ የሚሉት ተመስገንና አምደኞቹ በዋናነት የሚያቀርቡት ምክንያት ደግሞ “አኬልዳማ” የተሰኘውንና በኢቲቪ ለእይታ የበቃውን ዶክሜንተሪ ፊልም ነው፡፡ ፊልሙ በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ  የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችና አባላትን እንዲሁም ጋዜጠኞችን መብት የሚጋፋ፤ ከፍርድ ቤት ውሳኔ ቀድሞ ጥፋተኛ ብሎ የፈረጀ “ ሊበሏት ያሰቧትን” አይነት ቅድመ ውሳኔ ነው ።ይህ ደግሞ የፍርድ ቤቱን ነጻነት መጋፋት ነው የሚል ነው፡፡

“መለስ ዜናዊ ከመይ ቀኒዮ” የሚለው የተመስገን መጣጥፍ በፍትህ ጋዜጣ ላይ ለንባብ የበቃው ከአኬልዳማ ዶክመንተሪ ፊልም ዕይታ በፊት ነው፡፡ ይህ መጣጥፍ ስለምን ያወራናል ከተባለ ደግሞ እነ ርዕዮት አለሙና አንዱአለም ተጠርጣሪ ናቸው የሚል እንዳይመስላችሁ፡፡ የሚለው፦ እነዚህ ጋዜጠኞችና የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ነጻ ናቸው የሚል መጣጥፍ ነው፡፡

አኬልዳማ የተሰራው ህዝብ እንዳይደናገርና የፍርድ ቤቱን ነፃነት ቀድመው እንደነተመስገን ያሉ "ጋዜጠኞች" እና "ጋዜጦች" ተጠርጣሪዎቹን ነፃ ናቸው ብለው በማወጃቸው ነው፤ ብለው ጠቅላይ

ሚኒስትሩ እና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚንስትሩ ለፓርላማው አብራርተው እንደነበር እናስታውስ! ተመስገን በዚህ መጣጥፉም ሆነ በሌሎቹ እኛ ስንናገርና ስንጽፍ ትክክል ነን፤ መንግስት ወይም ከነሱ አመለካከት የተለዬ ነጻ ሃሳብ ያለው ሰው ሲናገር ደግሞ የፍ/ቤት መብት ተጥሷል ማለትን የለመደና በባዶ ሜዳ የሚፈነጭ ጥገኛ መሆኑን መገንዘብ ከባድ አይሆንም፡፡

የብሄር ብሄረሰቦችን መብት “የጭፈራና የዳንስ መብት” መረጋገጥ ሲል የሚያላግጠው ተመስገን፤ ቋንቋን መሰረት ባደረገው ፌዴራላዊ ስርዓት ላይ ሳምንት ከሳምንት የሚሳለቀው ተመስገን፤ ጭር ያለውን መንደር ለማቃለጥ ስላስፈለገው ብቻ የግብር ስርዓቱን “ነጠቃ” ነው ብሎ ለማጋነን ከሚጠላቸው ብሄር ብሄሰቦች ስር በዚሁ መጣጥፉ ሲወሸቅ ማየታችን ደግሞ የተመስገንን ድብቅ አጀንዳ ያረጋግጥልናል፡፡ “. . . . ይሄ ከብሄር ብሄረሰብ መብት ያለመከበርም ሆነ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመጠቀም መብት ከመገርሰስ የበለጠ ለቁጣ የሚያነሳሳ ነው” ገጽ 63

በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመጠቀም መብት መገርሰስ አለበት፣ ህዝቡ እየጮኸ ነው፤ የብሄር ብሄረሰብ መብት መከበር የለበትም ፤ኢትዮጵያዊነታችን መቅደም አለበት ሲል ህዝቡ ተቆጥቷል። ብሎ የሚዘምረውና የሚያቀነቅነው እራሱ ተመስገን እንዳልነበር ሁሉ የግብር ስርዓቱ ከነዚህ መብቶች ያለመከበርም በላይ ለቁጣ የሚያነሳሳ ነው በማለት ቢያንስ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ያለመከበር እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ገቢራዊ አለመሆን ለቁጣ እንደሚያነሳሳ ማመኑ ገጽ ሳይዘል እዛው በዛው ከራሱ ጋር የሚጋጭ ውል የሌለው ልቃቂት መሆኑን የሚያሳየን ነው፡፡

ወደሌላው ርዕሰ ጉዳይ ስንሻገር ተመስገን ደርሶ በማይመለከተውና በማያውቀው የሃይማኖት ጉዳይ ውስጥ ገብቶ የተንቦራጨቀበትን ርዕሰ ጉዳይ እናገኛለን፡፡ ርእሱ "ይድረስ ለአቡነ ቀውስጦስ የአዲስ አበባ ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ"ምነው አባታችን *እያወቁ..."የሚል "ምክር" አዘል ደብዳቤ ነው።*

የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ እንደማንኛውም ኢትዮጵያውያን ግለሰቦችና ተቋማት ለዘመናት ሲናፍቀን እና ስንፈራው፣ የቁጭት ክራር ስንከረክርለት እና ግጥም ስንደረድርለት ሽራ ስንወጥርለት ለኖርነው የአባይ ግድብ እውን መሆን ሁሉም የበኩሉን ይወጣ ዘንድ ያስተላለፉትን ጥሪ በመንተራስ ነው ተመስገን በዚህ መጣጥፉ ሊቀ ጳጳሱን ምክር ያሻዎታል የሚላቸው፡፡

በአባይ ጉዳይ ያልተቆጨና የማይቆጭ ኢትዮጵያዊ እንደማይኖር የሚገነዙቡት ሊቀጳጳስ “በአባይ ጉዳይ ላይ የሚያፈገፍግ ካለ ኢትዮጵያዊነቱ ተሰርዟል” የሚል ቁጭታዊ ትርጉም ያለው መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡ ተመስገንም “ ኢትዮጵያዊነቱ ተሰርዟል” የምትለውን ሀረግ መዞ” በየትኛውም አለም የመንግስትን እቅድ መደገፍም፤ መቃወምም እኩል መብት ነው፡፡ መብት የማይሆነው ለአንድ አገር ጠላት መተባበር ወይም ጥቅምን የሚጎዳ ተግባር መፈጸም ወይም የራስ ሀገርን ለሌላ ሀገር መሰለል ብቻ ነው” ይለናል፡፡ ገጽ 85

በርግጥ ሊቀ ጳጳሱ “ ኢትዮጵዊነቱ  ተሰርዟል፡፡" ሲሉ የዜግነት መብት የመስጠትና የመንሳት መብት ኖሯቸው እንዳልሆነ፤ የጉዳዩን ክብደትና የግላቸውን ጫፍ የነካ ለመግለጽ የቁጭት ስሜት ፈንቅሏቸውና ለመልዕክታቸውም አጽንኦት በመስጠት የተናገሩትና እንድምታውም እንተባበር የሚል እንደሆነ ተመስገን "ጋዜጠኛ" ከሆነ ይጠፋዋል ብዬ አላስብም፡፡ ዳሩ ተመስገን ጋዜጠኛ አይደለምና ማን መብት ሰጪ እና ነሺ አደረጎት ሲል ግብረገብ በጎደለው አማርኛ ሊቀጳጳሱን ውጉዝ ከመአርዮስ  ይላቸዋል ፡፡

በራሱ የመብት አስተያየት እንኳ ጉዳዩን ብናነጥረው  ከተቃዋሚው ጎራ ያልሆኑትንና ከናንተ ጋር ያላበርነውን ግለሰቦች የኢትዮጵያዊነት ዜግነታችንን በጋዜጣህ ስንት ጊዜ መንሳትህን ምነው ዘነጋኸው።  ዜግነት የመስጠትና የመንሳት መብት ከቶ ማን ይሆን ላንተ የሰጠህ? ለህዳሴው ግድብ ቦንድ የገዙ ባለሀብቶችን፣ ለህዳሴው ግድብ ኳስ የተጫወቱ አርቲስቶችን---- ስንቴ ነው ዜግነታቸውን በጋዜጣህ የነጠቅከው? ሊያውም ያንተ በግልጽ የቀረበ ዜግነትን የሚነሳ አማርኛ የቀረበ መሆኑንስ ወደኋላ ተመልሰህ ለማስታወስ ለምን አልፈቀድክም?

ለጠላት የተባበረውና እየተባበረ የሚገኘው፣ ለሌላውስ ሃገር እየሰለለና እያሰለለ የሚገኘው መንደር የትኛው ነው?ባይሆን ቀያፋውም አንተ፣ ሄሮድሱም አንተና አምደኞችህ እንጂ አቡኑ ስላልሆኑ ባይሆን ለናንተ "ጌታሆይ የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ብዬ ፀልያለሁ።

ተመስገንና በዙሪያው የሚገኙ |ነፃ´ጋዜጠኞች ለቋንቋ አጠቃቀማቸው ደንታ የሌላቸው፤ ግብረገብነትና ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ፈጽሞ የማይስተዋልባቸው ቢሆኑም |መርዶነጋሪ´ "ያለፈውን ስርዓት ናፋቂ´ ሲባሉ ይደብራቸዋል።

እነ ተመስገንን "ያለፈውን ስርዓት ናፋቂ "ከሚሉ ወገኖች ውስጥ ደግሞ አንዱ እኔ ነኝ። በርግጥም ያለፉትን ስርዓት ናፋቂ ስለመሆናቸው ደግሞ ከዚሁ የመጣጥፍ ጥርቅም ውስጥ የሚገኘው |የሃውልቱ ስር ፖለቲካ´ በሚል ርዕስ የተፃፈውና የጀነራል ሳሞራ የኑስን ጀነራልነት የሚኮንነው መጣጥፍ ያረጋግጥልናል። |የዛሬን አያድርገውና መቼም የወታደርን ያህል ክብር ያለው ሙያ የለም ነበር´ ገጽ 88 የሚለን ተመስገን "ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ" ገጽ 96 በማለት ላለፈው ስርዓት ቅኔ መወድሱን በማቅረብ ደምድሟል። ታዲያ ስለ ምንድነው ያለፈው ስርዓት ናፋቂ ስትባሉ የሚቆጠቁጣችሁ? አይገባኝም።

|የተከበሩና የቀለሉ መሪዎች´ በሚል የሚቀጥለው የመልስ  አምልኮ የመጣጥፍ ጥርቅም የተመስገንን የቀለለ |ጋዜጠኛ´ መሆን ያሳየናል። ቀድሞውኑ የቀለለ መሆኑን የሚያረጋግጠው ርዕሰ ጉዳዩን የመረጠበትን ምክንያት ሲያብራራ ነው። ከቅንነት ነው ርዕሰ ጉዳዩን ለማንሳት የፈለኩት ብሎ "ቅንነቴን ቅንቅን አድርጎ የሚያስብ ካለ -----"ይህ አገላለጹ ቅንቅን እንጂ ቀና አለመሆኑን የሚያውቁ

እንዳሉ የሚያረጋግጥ ነው። የቀለሉ መሪዎቹን ለመግለጽ የተከበሩ መሪዎችን ማሳያ አድርጎ ማህተመ ጋንዲን ይዘክራል።

"በህንድኛ satayagrha እየተባለ የሚጠራው የጋንዲ ሰለማዊ ትግል ስልት ፍፁም ከጥላቻ እና ከበቀል የፀዳ ------" ገጽ 99 መሆኑን የሚነግረን ተመስገን ||ጋንዲ አንድም ህንዳዊ ሃላፊነቱ "መብቱን መጠየቅ እንጂ መብቱን የነጠቁትን እንግሊዛውያን መጥላት´ እንዳልሆነ አስተምሯል´ በርግጥም ማህተመ ጋንዲ የሰለማዊ ትግል መገለጫ የሆነና የተከበረ መሪ ነው። ተመስገንም የተከበረ መሪ የሆነውን ማህተመ ጋንዲ አርአያ ሊሆንንይገባል አይነት መልዕክት ለማስተላለፍ የፈለገ ይመስላል። ግን ደግሞ መጀመሪያ እንደማህተመ ጋንዲ ሁኑ የሚል አካል እራሱ በመሆን ቢጀምር ምክሩን የበለጠ ውጤታማ ያደርገዋል።

ተመስገን ደሣለኝ መብታችን ተነፍጓል ያሉ የአዋልያው ኮሚቴ አካላትን መብታችሁን ጠይቁ ሲል በጋዜጣው አልመከረም፤ ይልቁንም "በጥብጡ አጋጣሚውን በመጠቀምም መንግስትን መንግሉ አመጻውን ከዳር እዳር አዛምቱ" አለ እንጂ።

የዋልድባ መነኮሳትንም በመስቀላችሁ ሰላምን ስበኩ ሳይሆን ያለው ተዋጉበት አለ እንጂ፤ የጉራፈርዳ ተፈናቃዮችንም "ደቡብ ላይ ዝመቱበት" እንጂ መብታችሁን በሕግ አግባብ ጠይቁ፤ አግባብ ያላቸው አካላትና ባለጉዳዮቹ ራሳቸው በጋራ ይውያዩና ችግሩን ይፍተቱ ሲል አላየሁም። ይልቁንም "መብታችንን ነጥቆናል "የሚለውን ኢህአዴግን እና አባላቱን የወረድሽ እለት ወዮልሽ እያለ በማስፈራራት ላይ ነው። ታዲያ ከእንዲህ አይነት በቀለኛ |ጋዜጠኛ´ በላይ የቀለለ የሚባለው ወይም |ቅንቅን´ የሚሆነው ማነው?

"ልጆቻችሁ ቻይና ምን አየሰሩ ነው" በሚለውና መተካካትን በተመለከተው መጣጥፍ የቀረበው ሁሉ የተመስገንን ነውረኝነት በግልጽ የሚያሳይ፤ የድርጅታዊ አካሄዶችንና አሰራሮችን ያላገናዘበ ጭፍን የቃላት ጥርቅም ብቻ ነው። ኢህአዴግ ማለት ከፍተኛ አመራሩና ልጆቻቸው ናቸው ብሎ ማሰብና ስልጣን በዕድል ነው የሚገኘው አይነት ይዘት ያለው የተዛባ ትንተና መስጠት ያላዋቂ ሳሚ እንዲሉ ነው። |መሰረታዊ ስህተት እስካልፈፀመ ድረስ ኢህአዴግ ከዚህ በኋላም ረዘም ላለ ጊዜ በስልጣን የመቆየት እድሉ የሰፋ ነው´ ገጽ 108

ከአዲሰ ራዕይ የተወሰደው የዚህ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ ግልጽ ይመስለኛል። በሃገራችን የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፕሮግራም የሌላቸው፣ ህዝብን ማዕከል ያላደረጉ በተለያየ መልኩና ደረጃ ከእርስ በርስ ሰጣ ገባ ያልወጡና እራሳቸውንም ማሸነፍ ያልቻሉ በመሆናቸው፤ ኢህአዴግ በአንፃሩ የተሻለ ልማት እያመጣ ከልምዶቹ እየተማረና ደረጃ በደረጃ ችግሮቹን እየፈታ የሚሄድ፤ በዚሁም የህዝብ ተቀባይነትን እያገኘ ፣ዓለም አቀፍ ግንኙነቱም እየጠነከረ መምጣቱን፣ የሚጎድሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ግን በመሰረታዊነት እየፈታ ካልሄደ በስተቀር ከላይ በቀረቡት አዎንታዊና

ተጨባጭ ስራዎች ምክንያት በተቃዋሚዎቹ ደካማነትም ምክንያት፣ የኢህአዴግ ረዘም ላለ ጊዜ የመመረጥ እድል የሰፋ ይሆናል ማለት ነው።

ተመስገን ግን ይህን ጽንሰ ሃሳብ ከከፍተኛ አመራሮች ልጆቻቸውን የመተካት ጉዳይ ጋር የሚያያዝ "ፍየል ወዲህ..." አይነት ትርጓሜ ሰጥቶ የጅላጅል ሙግት ለመግጠም ይሞክራል። "ክቡራትና ክቡራን በበዓል ዋዜማ ብዙ ላሰለቻችሁ ስለማልፈልግ ነገሬን እዚሁ ላይ ላብቃ።´ገጽ 111 ያንተ ነገር ከበዓሉም በፊት አሰልቺ መሆኑን በማመንህ ተራ ምስጋና ብንቸርህም ከባዶ ሃሳብህ፤በተለይም ከሁል ጊዜም " እልቂትና ፍጅት አውርድ" ዲያብሎሳዊ አመለካከትህ፤ምኞትህና ጥሪህ ልትላቀቅ ባለመቻልህ ታዘብንህም አዘንብህም።

የመለስ አምልኮ የሚለው የሁለተኛው ክፍል የመጨረሻ መጣጥፉም የዚሁ የተመስገን ስርዓት አልበኝነት እና ነውረኝነት መገለጫ ነው። እንዳልኳችሁ ተመስገን ከራሱም ጋር ጭምር ሲላተም አያውቀውም እንጂ ፍትህ ከተመሰረተች ጀምሮ ለህዝቡ የማይቀርብ፣ ከህዝብ ጋር የማይገናኝ፣ ዜጎቹን የማያበረታታ፣ የማይሸልም፦ "መሪ ሳይሆን መሰሪ ነው" ሲል በአንድ በሉ አምዱና በርዕሰ አንቀጹ ጽፎ አስነብቦናል።

ይህን የዘነጋው ተመስገን የጠቀላይ ሚኒሰትሩን ከህዝብ ጋር መገናኘት፣ ብርቱዎችን መሸለም፣ በየደረጃው ከሚገኙ ወጣቶች ሴቶችና ሌሎች ማህበራት ጋር መወያየትና ያጋጠሙ ችግሮቸን በጋራ ለመፍታት የሚያደርጉትን ጥረት፤ ሁሉ በማንኳሰስ" እራሳቸውን የመገንባት አምልኮ" ነው ብሎ ድምዳሜ ይሰጣል። እንዳው ስለእውነት ለመናገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከታወቁም የተጠየቁትን ሁሉ በተጨባጭ ማስረጃዎች በመመለስና በማብራራት እንጂ ተመስገን እንደሚለው "መለስ ይናገራሉ እንጂ በጥያቄ አይፋጠጡም" በሚል በገጽ 114 ያሰፈረው ሃሳብ መገለጫቸው ሊሆን በፍጹም አይችልም፡፡

የአፍሪካ ብቸኛ መገለጫ መሆን የሚቻለው ተመስገን ባለው መንገድ ወይስ በስራ ነው? ቤቱን የማይመራ እድር እንደማይመራው ሁሉ ሃገሩን በሚገባ ያላስተዳደረ መሪ የአህጉር መገለጫ መሆን ከቶ እንዴትስ ይቻለው ይሆን? ተመስገን እንደሚለው በሴራና እራስን በመገንባት ይቻል ይሆን? በፍፁም የማይመስል፤ እራስን በመገንባት መሆን የሚቻል ከሆነም የሚቻለው ምናልባት በህልም አለም ወይም በተመስገን ፍትህ ጋዜጣ ላይ ብቻ ነው።